# ዕይታ

2ኛ ዓመት ቁጥር 6

ሰኞ ሰኔ 14 ቀን 1985 ዓ.ም

የአንዱ ዋጋ ለአ/አ 75 ሣ.

ለክ/ሀገር 80 ሣ.


በውስጥ ገጾች


ገጽ 2 – የአፍሪካ አንድነትና የአፍሪካ መንግሥታት
– ሙጋቤ የአየር ላይ መሪ
3 – የፈላሻዋ ልጅ ተዓምር
– ኮምፒውተርና የሠራተኛ ዕድል
4 – ኢትዮጵያና ሶቭየት በጦር ሽመታ ዕዳ
5 – በየምግብ ቤቱ ያለው ይታወቅልን፤
6 – የራፍሳንጃኒ ቃለ ምልልስ – የቀጠለ
7 – ልብወለድ የመጀመሪያው ክፍል


## አሥራ አንድ የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በዋስ ተፈቱ

"ዕይታ በግንቦት 30 ቀን 1985 ዓ.ም ዕትሟ የታሰሩ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ውሳኔ በይደር" በሚል ርዕስ ግንቦት 26 ቀን በቀጨኔ አውራጃ ፍ/ቤት ተማሪዎቹ ቀርበው እንደነበርና ጉዳያቸው ተጣርቶ ባለመቅረቡ በሌላ ቀጠሮ ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ የወሰነ መሆኑን መግለጿ ይታወሳል።

በዚሁ መሠረት ሰኔ 10 ቀን 1985 ዓ.ም በተያዘው የቀጨኔ አውራጃ ፍ/ቤት ጊዜያዊ ቀጠሮ ጉዳያቸው ቀርቦ ከነበረው አሥራ አራት ተማሪዎች አሥራ አንዱ በዋስ የተለቀቁ መሆኑን ከሥፍራው የተገኘ ዜና ያመለክታል።

የተማሪዎቹን ጉዳይ የተመለከቱት ዳኛ በዕለቱ በዋስ ለተፈቱት ተማሪዎች እስካሁን ያባከኑትን የትምህርት ጊዜ ወደኋላ ተመልሰው እንዲያስታውሱና ለወደፊቱም ከዚህ መሰል ተግባር ተቆጥበው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ምክር ሰጥተዋል።

በዚሁ ዕለት በዋስ የተፈቱት ተማሪዎች

1) ተማሪ ሀብታሙ አለባቸው
2) " ማንደፍሮ ጥሩነህ
3) " ኪኒኒ ወ/ማርያም
4) " ይስሐቅ ደቆ
5) " ጥላሁን ዳኘ

በ5ኛው ገጽ ዞሯል

## ለእውራን ተማሪዎች ፖሊሲ የመቀረጹ አስፈላጊነት

በትምህርት ሚኒስቴር ድጋፍ ሰጪነት እየተረዱ ለሚማሩት ዕውራን ተማሪዎች ፖሊሲ መቀረጽ እንዳለበት የሰበታ መረሃ ዕውራንና የማዕከላዊ ብሬል ቤተመጻሕፍት ዐይነሥውራን ተማሪዎች ኮሚቴ ዋና ፀሐፊ ተማሪ ዳንኤል ሞላልኝ ለዕይታ ገልጧል።

ከልመናና ከመሳሰሉት አሳዛኝ ሕይወት ወጥተው በመንግሥት አማካኝነት የተሰባሰቡ ናቸው። ተማሪዎቹ ቤተሰብ የሌላቸው በመሆኑም፤ በመንግሥት ቁጥጥር በአዳሪ ተማሪነት እስከ 6ኛ ክፍል በአስፈላጊ ነገር ሁሉ እየተረዱ ይማራሉ።

በ4ኛው ገጽ ዞሯል



ተማሪ ዳንኤል ሞላልኝ

ከ300 በላይ የሚሆኑ ዕውራን ተማሪዎችን በመወከል ተማሪ ዳንኤል በሰጠው መግለጫ፤ ዕውራን ተማሪዎቹ፤

## የግሸን – መስከረም ታቦት

በዜና ማሠራጫ መሣሪያዎችና በልዩ ልዩ ጋዜጦች ተደጋግሞ እንደተገለጸው ይህች 1468 ዓመት ዕድሜ ያስመዘገበችው የግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም ገዳም ንዋየ ቅድሳት የሆነችው ፅላት ተሠርቃ በሽግግሩ መንግሥት የጥበቃ ኃይሎች ክትትል በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ከሌቦች እጅ ከተያዘች በኋላ የቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት ፅላቷን በሕጋዊ ደረሰኝ ተረክቦ በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስት ቅዱሳን ማርያም ቤተመቅደስ በጊዜያዊነት እንድትቆይ በማድረጉ ይህችን ፅላት ወደ ታሪካዊ ቦታዋ እንድትመለስ ለማድረግ በክልሉ ተወላጆች አስተባባሪነት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ጠንካራ ኮሚቴ ተቋቁሞ ጠቅላይ ቤተ ክህነትንም ሆነ የሚመለከተውን የመንግሥት አካል በመጠየቅ ጉዳዩን በንቃት ሲከታተል ከቆየ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ ፅላቷ እንድትመለስ ስለተወሰነ እነሆ ስለ ጉዞው መሳካት በዝግጅት ላይ እንገኛለን። ፅላቷም ወደ ግሸን የምትጓዘው ሰኔ 18 ቀን 1985 ዓ.ም በብፁዑ ወቅዱስ ፓትርያርክና ሊቃነ ጳጳሳት እንደዚሁም ብዛት ባላቸው ምዕመናን በክብር ታጅባ ነው።

የግሸን ደብረ ከርቤ ማርያም ገዳም በአጼ ካሌብ ዘመነ መንግሥት እንደተቆረቆረች ይነገራል■

## ከፓሪስ – አዲስ አበባ የሠላምና እርቅ ጉባኤ

ከመጋቢት 2 ቀን እስከ መጋቢት 4/1985 በፓሪስ የተሰበሰቡት 7 ተቀዋሚ ድርጅቶች ያሳለፉትን ውሳኔ መሠረት በማድረግ ሁሉን ያካተተ ሐገር አቀፍ የሰላምና የእርቅ ጉባዔ ከጥቅምት 5 እስከ 9/1986 ዓ.ም አዲስ አበባ እንደሚካሔድ የሰላም የዲሞክራሲና የእርቅ አስተባባሪ ኮሚቴ ሊ/መንበር የሆኑት ዶ/ር ነገደ ጐበዜ ገለጡ።

የጉባዔው ዓላማ የኢትዮጵያን ኅብረተሰብ የሚወክሉ ኃይሎች በሙሉ ተሰባስበው 55 ሚሊዮን የሚገመተው ሕዝብ እራሱን የሚገልፅበትን መድረክ እንዲፈጥር ለማድረግ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እንደሆነ ዶ/ር ነገደ ገልጸው፤ በጉባዔው የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ ከፖለቲካ ውጭ የተደራጁ ኃይሎች ተሳታፊ ሊሆኑ እንደሚችሉ አመልክተዋል።

የኮሚቴው ሊ/መንበር ስለ ጥቅምቱ የስብሰባ ጥሪ በሐገር ውስጥም ሆነ በውጭ ከፍተኛ ተቀባይነትና ድጋፍ መገኘቱን ገልጠዋል። በተለይም በውጭው ዓለም ድጋፉ ከተጠበቀው በላይ መሆኑንና ከዚህ ቀደም በአውሮፓ ፓርላሜንት አንድ ብሔራዊ ኮንፈረንስ እንዲደረግና በኢትዮጵያ ሕዝብ ተቀባይነት ያለው መንግሥት እንዲቋቋም ከተወሰነው በተጨማሪ በአሜሪካ ፓርላሜንትም ሆነ ኰንግረስ ባለፈው ሰሞን እንዲሁ ዓይነት ውይይት ተደርጐ እንደነበር ጠቁመዋል።

በተለይም ማዳም ማሪና ኦታዌ የተባሉ ምሁር ለአሜሪካ ኮንግረስ ባቀረቡት ጥናታዊ ዘገባ፤ ኮንፍራንሱ መደረግ እንዳለበትና ካልተደረገ ግን ኢሕአዴግ ገብቶ ምርጫ አካሒዳለሁ የሚለውን ካካሔደ እንዳለፈው ጊዜ ወጥመድ ውስጥ መግባት የለብንምና የታዛቢዎች ቡድን መላክ የለበትም እስከማለት መድረሳቸውን ገልጠዋል።

ዶ/ር ነገደ አክለውም ኢሕአዴግ እዚህ ስብሰባ ላይ አልገኝም አለ፤ ይሔ ስብሰባ አዲስ አበባ ላይ አይደረግም አለ

በ6ኛው ገጽ ዞሯል

## ውጣ ውረዱ በምድር ባቡር ድርጅት

የምድር ባቡር ድርጅት በመውሰድ ላይ ያለው የአስተዳደር እርምጃ የሠራተኛውን የሥራ ዋስትና እያሳጣው መሆኑ ከአንዳንድ ሠራተኞች የመጣ ጥቆማ ያመለክታል።

ድርጅቱ በኢትዮጵያና በጅቡቲ መንግሥታት የሚተዳደር መሆኑ ይታወቃል። ባለው ሰፊ ድርሻም ከፍተኛ የሥራ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ የሚገኙት በአዲስ አበባ ያሉት ሠራተኞች ላይ ያልተለመደና አግባብነቱ ያለየለት ድርጊት እየተፈጸመባቸው መሆኑ ተገልጧል። የሥራ ዝውውር በማድረግ፣ የረጅም ጊዜ የዕረፍት ፍቃድ እየሰጡ ከመደበኛ የሥራ ደረጃ በማንሳት ወዘተ. ሠራተኛውን ይህች ባቄላ ካደረች ላትቆረጠም ነው፤ ያሰኘው ጀመር።

በተለይም ካለፉት ሦስት ወራት ወዲህ ይህ ሁኔታ እጅግ ተባብሶ በሠራተኛው መካከል ልዩነት እንዲፈጠር የሚደረገው ግፊት አሳሳቢ እየሆነ በመምጣቱ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ

በ4ኛው ገጽ ዞሯል

## ጀርመን ተወለዱ፤ በጀርመን ነደዱ

ከሁለት ሳምንታት በፊት ሶሊንገን (ጀርመን) ውስጥ አፍቃሪያነ ናዚዎች በአንድ የመኖሪያ ሕንጻ ላይ በለኰሱት እሳት አምስት ሴቶች በቃጠሎው ሕይወታቸውን ማጣታቸው ይታወሳል። ይኸው አሰቃቂ ግድያ በጀርመን ውስጥ ከፍተኛ ውዝግብ ከማስነሳቱም በላይ ከዓለም አካባቢም ተቃውሞ አስከትሏል።

የናዚ ደጋፊ ነን ባዮች ያደረሱትን ጉዳት አስመልክቶ የተለያዩ ሐገር ጋዜጦች እንደሚከተለው ዘግበዋል። "የናዚ ቅሪቶች ሌላ ኢሰብአዊ ወንጀል ሰሩ። ሦስት ሴትና ሁለት ልጃገረዶችን ሕይወት በማቃጠል" ሁሪየት ጋዜጣ (ቱርክ)

"ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ በዘረኞች ትልቁ የደም ጠብታ ያረፈባት ሶሊንገን ለመሆን በቃች። ይህ የሚያመለክተው የደም መፋሰሱ የመጨረሻ አለመሆኑን ነው።" ኔዛቪሲማያ ጋዜጣ (ሩስያ)

"ብሔረተኝነት አደጋ በማድረስና በግድያ ልዩነት አያደርግም። የሶሊንገኑ ግን የለየለት ዘረኝነትና አሰቃቂ ነው። ይህ ደግሞ ለጥፋት የተነሳሱ ኃይሎች ከቁጥጥር ውጭ እየወጡ ለመሆን

በ5ኛው ገጽ ዞሯል



አምስት:- ሕይወት ያጠፋው የጀርመን ቃጠሎ

## የኢትዮጲስ ጋዜጣ ክስ ተቀሰቀሰ

በኢትዮጲስ ጋዜጣ ላይ በዐቃቤ ሕግ የተመሠረተውን ክስ ለማየት የማዕከላዊ ከፍተኛ ፍ/ቤት ስልጣን የለኝም በማለት የዘጋውን ፋይል እንዲያንቀሳቅስ በማዕከላዊ ጠ/ፍ/ቤት 2ኛ ወንጀል ችሎት ውሳኔ ተሰጠ።

ሰኔ 8 ቀን 1985 በዋለው ችሎት የማዕከላዊ ጠቅላይ ፍ/ቤት 2ኛ ወንጀል ችሎት ይህንን ሊወስን የቻለው በማ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ዐቃቤ ሕግ ያቀረበውን ይግባኝ ከመረመረ በኋላ ነው። ችሎቱ በሰጠው ውሳኔ "ማዕከላዊ ከፍ/ፍርድ ቤት የአዋጅ ቁጥር 34/1985 አንቀጽ 21/2/ን ድንጋጌ ከቃሉ አግባብና ከተግባራዊ ተፈፃሚነቱ ጋር ሳያገናዝብ የቃልን ተራ

በ4ኛው ገጽ ዞሯል

## በኢትዮጵያ እርምጃ ዩጋንዳ አቤት አለች

የዩጋንዳ መንግሥት ከኢትዮጵያ የተባረሩትን ዲፕሎማት ጉዳይ አስመልክቶ አቤቱታ ማሰማቱን የዩጋንዳ ሬድዮ ባለፈው ሳምንት ባሰራጨው ዜና ገለጠ።

ይኸው በሬድዮ የተሰማው የዩጋንዳ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ "በአዲስ አበባ የዩጋንዳ ኤምባሲ አንደኛ ፀሐፊ በሆኑት ዲፕሎማት ላይ የቀረበው ክስ የዩጋንዳ መንግሥት አልተቀበለውም። በጉዳዩም ላይ ክትትሉ እንደቀጠለ ነው" ይላል።

በሽግግር መንግሥቱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የወጣ መግለጫ በዩጋንዳ ኤምባሲ አንደኛ ፀሐፊ የሆኑት ሚስተር ሴቤሩምቢ ኪሴንዚጉ ከአንድ ዲፕሎማት በማይጠበቅ ሁኔታ የኢትዮጵያንና የዩጋንዳን ግንኙነት በሚያጐድፍና የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚነካ ተግባር ላይ ተሰማርተው በመገኘታቸው በ24 ሰዓት ውስጥ ከሐገር እንዲወጡ ሲል ያመለከተ መሆኑ ይታወሳል■

